በፌደራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን ለአዳዲስ የማረምና ማነፅ ባለሙያዎች ስለስራ ትውውቅ ስልጠና የተዘጋጀ ሰነድ

ጥር 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

Rule and regulation of trainers

- dignity and respect
- No disturbance (Mobile phone)
- AGREE to disagree
- Follow the agenda
- Participation
- Provide honest feed back
- Reflection

Cont…

- 2:20-4:30 first lecture
- 4:30-5:00 tea break
- 5:00-6:20 training
- 6:20 -8:00 lunch
- 8:00-9:15 group desiccations and presentations by trainees
- 9:15-9:45 tea break
- 9:45-11:00

መግቢያ

- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት ስለ ህግ ታራሚዎችና ቀጠሮ እስረኞች ከአንቀፅ 20 እስከ 23 አጠቃላይ ድንጋጌ አስቀምጧል።
- ከዚህ በመነሳት የፌደራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ መንግስት ህግ አስፈፃሚ ተቋም ሆኖ በአዋጅ **1174/2012** መሠረት ወንጀል ፈፅመዉ በፍርድ ቤት የተፈረደባቸዉን የህግ ታራሚዎችንና በቀጠሮ ማረፊያ ቤት እንዲቆዩ ትዕዛዝ የተሰጠባቸዉ እስረኞችን ተቀብሎ፡-
- **የተጠናከረ የጥበቃ፣ ደህንነት እና አስተዳደር፣**
- **የመሠረታዊ ፍላጎት አቅርቦቶችን በማሟላት እና**
- **የማረም ማነፅና ተሃድሶ ልማት አገልግሎቶችን በመስጠት የአመለካከት፣ የአስተሳሰብና የስብዕና እንዲሁም የባህሪ ለውጥ አምጥተው ከአጥፊነት እና ወንጀለኝነት ባህሪ ተላቀው አምራች፣ ሰላማዊና ሕግ አክባሪ ዜጋ እንዲሆኑ የማስቻል ዓለማ ይዞ የተቋቋመ ነዉ።**

- Empathy
- Sympathy
- Altruistic
- Egoistic

ይህን ዓለማ ለማሳካት የፌደራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን የሚከተሉትን ራዕይ፣ ተልዕኮ እና እሴቶች ቀርፆ በመሰራት ላይ ይገኛል።

ራዕይ

በ2022 ዓ.ም. መልካም አስተዳደር የሰፈነበት፣ የሕግ የበላይነትና የታራሚዎች ሰብዓዊ መብት የሚከበርበት፣ የታረመና የታነፀ፣ አምራችና ሕግ አክባሪ ዜጋ የሚፈራበት ተቋም ዕዉን ማድረግ።

ተልዕኮ

በፍርድ ቤት ውሳኔና ትዕዛዝ ወደ ማረሚያ ቤት የሚመጡ ታራሚዎችንና የቀጠሮ እስረኞችን በመቀበል፡-

- የተጠናከረ የጥበቃና ደህንነት አስተዳደር፣
- የተሟላ የመሰረታዊ ፍላጎቶች አቅርቦቶች፣
- የማረም ማነፅና ተሃድሶ ልማት አገልግሎቶችን በማከናወን ታራሚዎች

የወንጀልን አስከፊነት አውቀውና ተረድተው ከአስከፊነቱ ተምረው አምራችና ሕግ አክባሪ ዜጋ እንዲሆኑ በማድረግ ተቋሙ በወንጀል መከላከልና የህዝብን ሰላምና ደህንነት በማረጋገጥ የበኩሉን ድርሻ መወጣት::

እሴቶች

- የሕግ የበላይነት ማክበርና ማስከበር፣
- ሰብዓዊ መብት ማክበርና ማስከበር፣
- ፍትሀዊነትና አድሎ አለመፈፀም፣
- ኪራይ ሰብሳቢነትና ሙስናን መፀየፍ፣
- ግልጽነት እና ተጠያቂነት ማስፈን፣
- በታማኝነትና በቅንነት ማገልገል፣
- ማረምና ማነፅ ተኮር ተግባር ማከናወን፣
- ለለዉጥ ዝግጁነት፣
- አርአያነት ናቸው።

እላይ የተቀመጠዉን ዓላማ እና ተልዕኮ ለማሳካት የማረም ማነፅና ተሐድሶ አገልግሎቶችን ለሕግ ታራሚዎችና ቀጠሮ እስረኞች በምን አግባብ መስጠት እንዳለብን በንዑስ ክፍል ሦስት ስር በዝርዝር ተቀምጧል።
አንቀፅ 42 ስለማህበራዊና ምክክር አገልግሎት፣ አንቀፅ 43 የቀለምና የሙያ ስልጠና፣ አንቀፅ 44 ስለመልሶ ማቋቋም፣ አንቀፅ 45 ስለስራ ማሰራት፣ አንቀፅ 39 ስለስፖርታዊና አካላዊ እንቅስቃሴ እና መዝናኛ አገልግሎት አሰጣጥ በዝርዝር አስቀምጧል።

● የማረም ማነፅና ተሃድሶ ልማት ዘርፍ በተለይም ደግሞ የማረምና ማነፅ ዳይሬክቶሬት በታራሚዎች አስተሳሰብ፣ አመለካከትና ባህሪያቸዉ ላይ በመስራት እንዲረጋጉና፣ ለመታረምና ለመታነፅ ዝግጁ እንዲሆኑ፣ የአመለካከት፣ የአስተሳሰብና የስብዕና እንዲሁም የባህሪ ለውጥ አምጥተው ከአጥፊነት እና ወንጀለኝነት ባህሪ ተለቀው አምራች፣ ሰላማዊና ሕግ አክባሪ ዜጋ እንዲሆኑ የሚሰራ ነዉ።

እነዚህን ስራዎች ጥራት ባለዉ መልኩ ለሁሉም ተደራሽ በማድረግ የተቀመጠዉን ዉጤት ለማስመዝገብ እዉቀትና ክህሎት ያለቸዉ የሰዉ ሀይል ያስፈልጋል።

- ለዚህ ደግሞ አዳዲስ የሚቀጠሩ ባለሙያዎች ከተቋሙ አሰራር ጋር በጥልቀት በማስተዋወቅ ወደ ስራ ማስገባት አንዱ ስልት ነው።
- ስለዚህ ስልጠናዉ በባለሙያ ዕዉቀትና ክህሎት መዳበር ዙሪያ እና ስለተቋሙ አጠቃላይ ግንዛቤ ጨብጦ ወደ ስራ ለመግባት እና ውጤታማ ስራ ለመስራት አስተዋፅኦ ስላለው በትኩረት መከታተል ያስፈልጋል።

ክፍል አንድ

ስለማረም ማነፅና ተሃድሶ

(Correction and Rehabilitation)

አጠቃላይ ምንነት


ዘርፍ
ነዉ።
(Manif

ለወንጀለኛነት መነሻ የሆኑ ፅንሰ ሃሳቦች

1. Strain theory :-አንድ ማህበረሰብ ያስቀመጣቸውን የማህበረሰብ ወጎች ለማሳካት የወንጀል ተግባራትን መፈፀም ለምሳሌ ማግባት ፡ቤት መስራት ለማሳካት ገንዘብ ያጣና የወንጀል ተግባራትን መፈፀም ።
2. Control theory :-ከማህበረሰብ ጋር ጥሩ ግንኙነትና አብሮነት ካለን ወንጀል የመስራት ተግባራችን በጣም አናሳ ነው ለምሳሌ አርሶ አደር ማህበረሰብና በከተማ የሚኖር ማህበረሰብ
3. Theortical perspective :-ከቤተሰብ ተምረን የምነተገብረው ለምሳሌ አባት ለልጁ ሽጉጥ ገዝቶ ቢሰጠው እና ልጅ ገዳይ አባት ተገዳይ ጫወታ ቢጫወቱ ወደ ወንጀል ተግባር የማደግ ዝንባሌው ከፍተኛ ነው።

Symptoms of Abnormality

- Unusual of abnormality(ያልተለመደ ባህሪ ማሳየት)
- Aggression (ቁጡነት)
- Talkativeness (ወሬ ማብዘት)
- Laughing alone (ለብቻ መሳቅ)
- Sleeping disturbance (የእንቅልፍ መብዛት ወይም በቂ አለመሆን)
- Self neglect(እራስን አለመጠበቅ ለምሳሌ ልብስን አስተካክሎ አለመልበስ
- Restlessness (እረፍት ማጣት 72-80% hereditary)

3● ማህበራዊ ልማት (social development) (በት/ት እውቀታቸው፣ ክህሎታቸው ወዘተ ከፍ ማድረግ፣ **በኢኮኖሚ ራሳቸውን እንዲያሻሽሉ፣** በህይማኖትና በባህል ራሳቸውን ማጎልበት **እንዲችሉ** ለምሳሌ መቻቻል፣ መተጋገዝ፣ መረዳዳት፣ ወዘተ) እና ማህበራዊ ሀላፊነቶችን (ለምሳሌ የራሳቸውን፣ የቤተሰቦቻቸውን፣ የወገኖቻቸውን ለምሳሌ አብሮ ያሉ ሌሎች ታራሚ ወንድሞቻቸውን፣ በማዕከሉ ዉስጥ የሚያገለግሉ አባሎችንና ባለሙያዎችን **ማገዝ፣ማክበር)** እሴቶችን (ለሕግ ተገዥ መሆንና ማክበር፣ መረዳዳት፣ መተባበር፣ መፈቃቀር፣ የተጣላውን ማስታረቅ፣ የታመሙትን ማሳከምና ማስታመም፣ በወንድማዊ እህታዊ (ቤተሰባዊ) እይታ መተያየት...) የማጎልበት ስራዎችና ተግባራትን በውስጡ አቅፎ የያዘ እና የእነዚህ ተግባራት ሂደት ውጤት ነው።

4● ወደ ራሳቸው እንዲንመለሱ፣ ወደ ዉስጣቸው እንዲያዩ፣ ራሳቸውን እንዲፈልጉና እንዲሆኑ የማስተማር ሂደት ነዉ። ጥንካሬያቸውን፣ ክፍተቶቻቸውን፣ ችሎታቸውን እንዲያወጡ ማስቻል ነው።

5●በሰላም ከማህበረሰባቸው ጋር እንዲኖሩ (በማረሚያ ቤት ዉስጥና ተፈቶ ከወጡ በኃላም፣ ወደ ማህበረሰቡ በሰላም በመቀላቀል ሰላማዊ ኑሮ እንዲመሩ አቅም መፍጠር/ ማስገንዘብ ነው።

(የኃይል ጥቃት፣ ብጥብጥና ሁከትን የሚከላከል፣ የሚቆጣጠር፣ የሚቀንስ ወዘተ ውጤታማ ስትራቴጂ ሊኖረንና ከታራሚ ጋር በጋራ ሊንተገብር ይገባል)።

● በመኖሪያ ቤታቸው፣ በጋራ መገልገያ ሰፍራዎቻቸው፣ በስራ፣ በትምህርት፣ በስልጠና፣ በመዝናኛ፣ ወዘተ ቦታዎች አካላዊ፣ ስነ ልቦናዊ፣ የብሔር፣ የሀይማኖት፣ የቋንቋ፣ የባህል ወዘተ እኩልነትና ብዝሃነት ተከብሮላቸው ደህንነት፣ ምቾትና ሰላም ሊረጋገጥላቸው ይገባል።

እላይ የተዘረዘሩ የተሃድሶ ዓለማዎችን ለማሳካትና የተጠቀሱትን ዉጤቶች ለማግኘት መከናወን ያለባቸዉ ተግባራት፡-

- የጎልማሶች መሠረታዊ ት/ትና የቀለም ትምህርት፣
- የቴክኒክና ሙያ ስልጠናዎች፣
- የማህበራዊ ክህሎት ስልጠናዎችና የማህበራዊነት ግንባታ፣
- ስነ ልቦናዊ ምክክሮችና ግንባታዎች፣
- ልዩ ልዩ የባህሪ፣ የስነ ልቦና፣ የማህበራዊ፣ ሱስና ሱሰኝነት ወዘተ ችግሮችን ዳሶና ለይቶ ማረም፣

- የቤተሰብ፣ የጓደኛ፣ የቅርብ ዘመድ ትስስር (ግንኙነት) ማጠናከርን፣
- ስለ ስራ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ፣ ክቡርነት፣ ስለ መቀጠር፣ ስለ ስራ መፍጠርና ራስን በስራ ማበልፀግ ወዘተ ማማከር፣ ሀሳብ፣ እውቀት፣ ልምድ ወዘተ መለዋወጥ ይጠበቅብናል።
- የአካል ብቃት ስራዎችና እንቅስቃሴዎች፣
- መልካም ስነ ምግባራዊነትን ማጠናከር፣
- የእንክብካቤ ስራዎች ለምሳሌ ከገቡበት (ከጋጠማቸው) ችግሮች፣ አስጊ ሁኔታዎች፣ የሕይወት ጠንቆች ወዘተ ለማላቀቅ፣ ለማስወገድ፣ መመካከርና በውስጡ እንዲሳተፉ ማድረግ አለብን።
- የአገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማበረታታት፣ ማነሳሳትና መደገፍ አለብን።

እነዚህ ዝርዝር የተሃድሶ ውጤቶች የሚከተሉት ቁልፍ አገልግሎቶች **ቅንጅት ዉጤት** ነዉ።

1. **ማረም (Correction):-** የባህሪ፣ የአስተሳሰብ፣ የአመለካከት፣ የስብዕና ወዘተ ክፍተቶችና የወንጀለኝነት ፍላጎት ለይቶ እርምት፣ ጥንቃቄና ክትትል ማድረግ፣
2. **ልማት (Development):- እውቀት፣ክህሎት፣ ብቃትና ልምድን ማሳግ ላይ ትኩረት** የሚያደርግ ለምሳሌ፡- ማህበራዊ ልማት፣ ትምህርትና ስልጠና፣ ስራን ማሰራት፣ የመዝናኛ፣ የስፖርት አገልግሎቶች፣ ሐይማኖታዊና ባህላዊ፣ ስነ ምግባራዊ፣ ስነ ልቦናዊ ግንባታ ወዘተ
3. **ተገቢ አያያዝ (እንክብካቤ ማድረግ) (Care):-** ከቤተሰብ፣ ከዘመድ፣ ከሐይማኖት አባት፣ ከእርስ በርስ ወዘተ ጋር ያላቸው ግንኙነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል መስራት፣ አካላዊና አእምሯዊ ጤንነታቸውን መጠበቅ (በእንቅስቃሴ፣ በህክምና፣ በምክክር፣ በመዝናኛ፣ በስራ ወዘተ)፣ የምግብና ሂደት፣

4. ማህበራዊ ዉህደትን መፍጠር (Social Integration) ወይም ለመልሶ መቀላቀል ዝግጁ እንዲሆኑ ማድረግ፡-

- የማረምና ማነጽ ተግባራት መልሶ መቀላቀልን ትኩረት ያደረገ እና የማዕከሉ ማህበረሰብ (ታራሚዎችን ጨምሮ) ከአካባቢው ህብረተሰብ፣ ከቤተሰብ፣ ከዕምነት ተቋማት፣ ከታዋቂ ግለሰቦች፣ ከሃገር ሽማግሌዎች፣ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ወዘተ ጋር በቅንጅት መስራት፣ (ልማት ላይ በመሳተፍ፣ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ትብብር በማድረግ ወዘተ)
- ይህ ተግባር ዛሬ ላይ ሆኖ ከፊቹ በኋላ የሚናከናዉናቸዉን ተግባራትን ያጠቃልላል።

5. **ደህንነታቸውን መጠበቅ፡-** ይህ ሲባል በጣም ሰፊ ሀሳብና ተግባራትን በውስጡ ያካተተ ነዉ።

ለምሳሌ፡-

- በፈፀሙት ወንጀል በፍርድ ቤት ከተጣለባቸው ቅጣት በተጨማሪ መድሎ፣ መገለል፣ መሸማቀቅ፣ወዘተ ይደርስብኝ ይሆን ወዘተ፣ ስጋት ነጻ ማድረግ፣
- በዕድሜዬ፣ በጤና ፣ በአካላዊ ጉዳቴ፣ በት/ት ደረጃዬ፣ ደጋጋሚ በመሆነ፣ የዚህ ዘር፣ ብሔር፣ ሀይማኖት ተከታይ፣ ቋንቋ ተናጋሪ፣ ባህል ተከታይ ወዘተ በመሆነ ያጠቁኝ ይሆን፣ ያንቋሸሹኝ ይሆን፣ ይቀጡኝ ይሆን ወዘተ፣

● የተለየ የፖለቲካ አመለካከት፣ የተለየ ሀሳብና አስተያየት በመያዝ፣ ሀሳቤን በነፃነት በመግለፀ፣ ስለመብቴ በመከራከረ ወዘተ ማግኘት ያለብኝን ጥቅማ ጥቅም እከለከል ይሆን ብሎ መስጋት፣ መጨነቅ፣ ወዘተ ስጋቶች ነፃ ሆነው **ስነ ልቦናዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ አካለዊ ጤና ወዘተ** ደህንነቶቻቸውን መጠበቅ አለብን።።

1.2. በማረምና ማነፅ ዳይሬክቶሬት ስር የሚካተቱ ዝርዝር አገልግሎቶችና ውጤቶቻቸዉ

1. በማህበራዊ አገልግሎት

1.1. አዲስ ገቢ ታራሚዎችና የቀጠሮ እስረኞች የማረጋጋት ስራ መስራት፤

- ወደ **ማረሚያ ቤት የተላኩበት ዓላማ ግንዛቤ እንዲኖራቸዉ** ማድረግ፤

- ለታራሚዎች የፌደራል ማረሚያ ቤቶችን **ራዕይ፤ ተልዕኮና እሴቶች በማስገንዘብና ለስኬታማነቱ ደጋፊ እንዲሆኑና መብት እና ግዴታቸዉን የማሳወቅና እንዴት እንደሚወጡ** ስራ የሚሰራበት አገልግሎት ነዉ።

በዚህ ሂደት ዉስጥ ፡-

● ታራሚዎች ከማረሚያ ቤት የእርምት ስራ ጋር የማለመድና የእርምት እቅድ እንዲኖራቸው የማድረግ፤ ለእርምት ተግባራት የማነሳሳትና ማዘጋጀት ስራ ይሠራል።

● በማረሚያ ቤት ቆይታቸዉ በነፃ የሚያገኙት አገልግሎቶች ከጥበቃ ደህንነትና አስተዳደር፤ ከመሠረታዊ ፍላጎት ማሟላት፣ ከማረም ማነፅና ተሃድሶ ልማት እና ከፋይናንስ ሰው ሀብት አስተዳደር አንፃር ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ ይሰራል።

● እነዚህን መብቶቻቸዉን ለማስከበር ከህግ ታራሚዎችና ከቀጠሮ አስረኞች የሚጠበቀውን ግዴታ የማሳወቅ ስራ ይሠራል።

● የማረጋጋት አገልግሎት የማረምና ማነፅ ሙያዎችን ከሌሎች የስራ ክፍሎች ተግባራት ጋር በማቀናጀት የሚሰጥ አገለግሎት ነው።

● በአጠቃላይ ይህ አገልግሎት አዲስ ገቢ ታራሚዎችንና የቀጠሮ እስረኞችን በማረጋጋት **ሳይረበሹና ለአላስፈላጊ የስነ ልቦናና ማህበራዊ ችግሮች ሳይጋለጡ ማረሚያ ቤቱንና የማረሚያ ቤትን አሠራር በቀላሉ እንዲለመዱ** ያደርጋቸዋል።

● ይህ መሆኑ ታራሚዎች ካለመረጋጋት ለሚመነጩ **የማህበራዊ፣ ስነ ልቦናዊ፣ አእምያዊ** ወዘተ ችግሮች ለምሳሌ ከእርስ በርስ ግጭት፣ ከማረሚያ የፖሊስ አባላት ጋር መጋጨት፣ በአጠቃላይ ሁከት እንዳይፈጠር ይረዳቸዋል።

● የአገልግሎቱ ውጤትም በእነዚህ ይገመገማል።

1.2 የማህበራዊ አኗኗር ክህሎት ስልጠና

ለታራሚዎችና ለቀጠሮ እስረኞች በማረሚያ ቤት ቆይታቸዉ ወቅት የአኗኗር ክህሎት ስልጠና የሚሰጠዉ፡-

- **መልካም ማህበራዊ ግንኙነትንና ትስስርን በመፍጠር ለመታረምና ለመታነፅ ራሳቸዉን እንዲያዘጋጁ** ለማድረግ ነዉ።
- ታራሚዎች እርስ በርሳቸዉ **ከመጎዳዳት፣ ከመደባደብ፣ ከመጋጨት፣ ሁከት ከመፍጠር ወዘተ** በሚመነጭ ለተቋሙ መረጋጋት ስጋት የሚሆኑ ሁኔታዎች ለመቅረፍ ነዉ።
- የዚህ ስልጠና መሠረታዊ ዓላማ **ሰዎች ራሳቸውን አውቀው እና ሌሎችን ተረድተው ጥሩ ግንኙነት በመመስረት የተሻለ ሕይወት የሚኖሩበትን ሂደት እንዲፈጥሩ ለማስቻል** ነው።

● በማረሚያ/ማረፊያ ቤት ቆይታቸዉ ወቅትም ሆነ የእርምት ጊዜያቸዉን ጨርሰዉ ከሕብረተሰቡ ጋር በሚቀላቀሉበት ወቅት ታርመዉና ታንፀዉ፣ ከአጥፊነትና ወንጀለኝነት ባህሪ ተላቀው፤ ሠላማዊና አምራች ዜጋ ሆነዉ መልካም የሆነ ማህበራዊ ኑሮ እንዲመሩ የሚያስችላቸዉ ስልጠና ነዉ። በዚህ የማህበራዊ አኗኗር ክህሎት ስልጠና የሚካተቱ፡-

● ታራሚዎች ማህበራዊ ኑሮን እንዴት መመስረት እና መምራት እንደለባቸዉ፣

● ከሌሎች ሰዎች ጋር እንዴት ጓደኝነትና ትስስር (የስራ፣ የማህበራዊ ኑሮ፣ ወዘተ) መፍጠር እንደሚገባቸዉና እና ጠቀሜታዉን እንዲረዱ፣

● የአቻ ግፊትና የቡድን አሉታዊ ዉሳኔዎችን መ ssም እንዲችሉ ማድረግ፣

- በሂደትም እንዴት **የበጎ አመለካከትና ስብዕና ባለቤት** መሆን እንዲችሉ፣
- **በመልካም ማህበራዊ ኑሮ ግንባታ** ሂደት ውስጥ ያላቸውን ሚና እንዲወጡ፣
- **በሰዎች መካከል ያሉትን ዘርፈ ብዙ ልዩነቶች** (የአስተሳሰብ፣ የባህርና ፀባይ፣ የዕዉቀትና ክ
የኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች፣ የባህል፣ የቋንቋ፣ የፆታ፣ የዕድሜ፣ የጤና ወዘተ) በመዳሰስ እንዴት ሰ
ልገነዘቡና ልረዱ እንደምችሉ እና**ልዩነቶችን ማስተናገድ** እንዳለባቸዉ፣ ልዩነቶችን **በአግባቡ
አለማስተናገድ ለወንጀል ባህሪ ያለዉ አስተዋፅኦ** እንዲገነዘቡ፣
- **ተግባብቶት ለታራሚዎች ማህበራዊ ህይወት** ያለዉ ፋይዳ እና ሲጓደል ለወንጀል ባህሪ ያለዉ
አስተዋፅኦ፣
- ስለ **እርቅ ሂደት፣ እሴቶች እና እርቅ ወይም ስምምነት መኖሩን** የሚያመላክቱ ሁኔታዎች ሰ
መገንዘብ፣
- የዜጎች ማህበራዊ ተሳትፎ፣ የዜጎች መልካም ባህሪያት፣ የዜጎች መልካም ስነ-ምግባር እና ስለ
መቻቻል ስልጠና የሚሰጥበት የማህበራዊ አገልግሎት አካል ነዉ።

1.3 በየወቅቱ የሚከሰቱ ማህበራዊ ችግሮቻቸዉን መፍታት እንዲችሉ ግንዛቤ ማስጨበጥና የአቅም ግንባታ ስራ መስራት።

● ታራሚዎች በየወቅቱ የሚከሰቱ ማህበራዊ ችግሮችን በመለየት መፍትሄ እንዲያፈላልጉ በማድረግ በማረሚያ ቤት ቆይታቸዉ **የሚገጥማቸዉን ማህበራዊ ችግሮች መፍትሄ እንዴት ማፈላለግ እንዳለባቸዉ አቅምና ግንዛቤ የማስያዝ** ስራዎች ይሠራል።

● በማረሚያ/ማረፊያ ቤት ለማህበራዊ ችግሮች መፍትሔ ማፈላለግ መለማመዳቸዉና ክህሎት ማዳበራቸዉ ከማረሚያ ቤቶች ተፈተዉ ሲወጡም ያገለግላቸዋል።

1.4 ለተፈቺ የህግ ታራሚዎች ሊፈቱ ሲሉ የህይወት ክህሎት ስልጠና ይሠጣል።

- ለተፈቺ የህግ ታራሚዎች የህይወት ክህሎት ስልጠና በመስጠት ታራሚዎች **የልዩ ልዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ስነ ልቦናዊና አከባቢያዊ ወዘተ ክህሎቶች ባለቤቶች በመሆን** ተፈተዉ ወደ ማህበረሰቡ ሲቀላቀሉ ክህሎቶቹን በመጠቀም ለሚቀበለቸዉ ዓለም እንግዳና አዲስ ሳይሆኑ ተረጋግቶ በሰላም መኖር እንዲችሉና ቤተሰባቸዉን መምራት እንዲችሉ ያደርጋቸዋል።
- **ለመልሶ መቀላቀል ዝግጁ** ማድረግ ማለት ነው።

Strategies for Reducing Crime

1. Reduce social inequality and poverty.
2. Replace low-wage jobs with jobs that pay a living wage.
3. Prevent child abuse and neglect.
4. Increase the social and economic stability of communities.
5. Improve education in all communities.
6. Establish an integrated approach of social control mechanism that includes both formal and informal.

- የህይወት ክህሎት ትምህርት **አእምሮዊ፣ አካላዊ፣ ማህበራዊ፣ ስነ-ልቦናዊ እና አካባቢያዊ ክህሎቶችን በማስገንዘብ ዝግጁነታቸው ከፍ እንዲል** ያደርጋል።
- በመሆኑም እነዚህን ክህሎቶች በደንብ ማወቅና በትክክል ስራ ላይ ማዋል **አካባቢን በቀላሉ ለመልመድና ህይወትን በአግባቡ ለመምራት በማስቻል ሰዎች ከአካባቢያቸዉና ከማህበረሰባቸዉ ጋር ተስማምተዉ እንዲኖሩ** ያስችላል።
- ለታራሚዎች በማረሚያ ቤት ቆይታቸዉም ሆነ ከማረሚያ ቤት በሚወጡበት ወቅት **የተሻለ ህይወት እንዲመሩ** ይጠቅማቸዋል።

ታራሚዎች:-

- ራሳቸዉን እንዲያዉቁ፣ ለራሳቸዉ ክብር እንዲኖራቸዉ፣ ራሳቸዉን እንዲሆኑ የማስቻል፣ (ራስን ስለማወቅና ከራስ ጋር ተስማምቶ የመኖር ክህሎትን፣ ራስን ማወቅንና እሴቶቹን እና መገለጫዎቹን፣ ለራስ ተገቢ ክብርን ስለመስጠት፣ ለራስ ተገቢ ክብርን መስጠትን እንዴት ማዳበር እንደምንችል፣ ራስን መሆንና መገለጫዎቹን በማስገንዘብ)
- አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸዉ የማድረግ፣
- አዎንታዊ ስብእና እንዲኖራቸዉ የማድረግ፣
- ራሳቸዉን ከጎጂ ባህሪያት እንዲገቱ የማስቻል፣
- ስሜታቸዉን፣ ጭንቀታቸዉን እና ብስጭታቸዉን እንዲቆጣጠሩ (እንዲገቱ) የማስገንዘብ፣

- **ችግር የመፍታት ክህሎታቸዉን እንዲያዳብሩ ማድረግ፣** (ችግሮችን የመፍታት ሂደት፤ ክህሎት እና እሴት በማስገንዘብ)፣
የፈጠራ ክህሎታቸዉን እንዲያዳብሩ የማስቻል፣ (ፈጠራ የተሞላበት አስተሳሰብ ስልቶች፣ እሴቶች፣ መገለጫዎች እና መሰናክሎች)፣
- **በጥልቀት የማሰብ ክህሎታቸዉን እንዲያዳብሩ የማስቻል፣** (በጥልቀት የማሰብ፣ እሴቶች፣ መገለጫዎቹ እና በጥልቀት ማሰብ ወንጀልን ለመከላከል ያላቸዉ አስተዋጽኦ በማስገንዘብ)፣
- **ስነ ምግባራቸዉን እና ግብረ ገብነታቸዉን እንዲያሳድጉ የማስቻል፣** (ስነ-ምግባር እና ግብረገብነት ለታራሚዎች ያለዉ ፋይዳ በማስገንዘብ)፣
- **የስራ ክህሎታቸዉን እንዲያጎለብቱና እንዲያዳብሩ የማድረግ፣**

- የገንዘብ አያያዝ ክህሎታቸዉን እንዲያሻሽሉ የማስቻል፣ (ገቢን እና ጊዜን በአግባቡ የመጠቀም ክህሎት እንዲኖራቸዉ በማድረግ)፣
- ጊዜያቸዉን በአግባቡ የመጠቀም ክህሎት እንዲያጎለብቱ የማድረግ፣ ማ/ቤት ከገቡ ቀን ጀምሮ የእርምት እቅድ እንዲያወጡ ማድረግ አለብን።
- ያላቸዉን የግል ተሰጥዖ እንዲገነዘቡ እና እንዲጠቀሙበት የማስቻል፣
- ጤናማነታቸዉን የሚያጎለብቱ አካላዊ እንቅስቃሴና መዝናኛዎችን እንዲያከናዉኑ የማስገንዘብ፣
- ወደ ዳግም ወንጀል ሊያስገቡ የሚችሉ ድርጊቶችን እንዲለዩና እንዲያስወግዱ የሚችሉበትን ሁኔታ እንዲያበለጽጉ የሚረዷቸዉን ክህሎቶች እንዲያሳድጉ የማስቻል፣

- ታራሚዎች ስለህይወት ክህሎት **መርሆዎች (principles) እና ተግባሮች (Practices) እንዲገነዘቡና** በህይወታዊ ጉዞአቸዉ ዉስጥ ተግባራዊ እንዲያደርጉ የማስቻል፣
- **ግጭትን በሰላማዊ መንገድ የመፍታት ክህሎት እንዲያዳብሩ የማድረግ**፣ ወዘተ ስልጠናዎች የሚሰጥበት አገልግሎት ነዉ።
- **ውጤቶቹንም ከእነዚህ ነጥቦች አንፃር መገምገም ይጠበቃል።**

2. የምክክር አገልግሎት

በሁሉም የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ስር ለሚገኙ ማዕከል ማረሚያ ቤቶችና ማረፊያ ቤቶች ከዚህ በታች የተዘረዘሩት የምክክር አገልግሎት አይነቶች ይሰጣሉ።

እነዚህም፦

1. የቅድመ መከላከል የምክክር አገልግሎት፣
2. የተናጥል (የግል) የምክክር አገልግሎት፣
3. የቡድን (የጋራ) የምክክር አገልግሎት፣
4. የአቻ ለአቻ የምክክር አገልግሎት፣

2.1 የቅድመ መከላከል የምክክር አገልግሎት

- የህግ ታራሚዎች/ የቀጠሮ እስረኞች ከቤተሰባቸዉ፣ ከዘመድ አዝማዳቸዉና ከለመዱት አካባቢ ፍፁም ወደማያዉቁት አካባቢ ማለትም ማረሚያ/ ማረፊያ ቤት ሲገቡ ለስነ ልቦና ቀዉሶች ይዳረጋሉ።።
- እነዚህ የስነ ልቦና ቀዉሶች የአንድን ሰው ስብዕና፣ አእምሮ፣ ሀሳብ፣ ባህሪ፣ ስሜት፣ አመለካከት፣ እውቀት፣ አስተሳሰብ ወዘተ በከፍተኛ መጠን የሚጎዱ አእምሯዊ ችግሮች ናቸዉ።

● በሰዎች ላይ የጭንቀት፣ የፍርሃት፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ስቃይ፣ ሀዘን፣ ድብርት፣ ትካዜ፣ ግራ መጋባት፣ ቁጣ፣ ስሜታዊነት ወ.ዘ.ተ ችግሮችን የሚያስከትሉ ናቸው።

● የአእምሮ ህመም በመሆናቸውም አንድ ግለሰብ የዕለት ተዕለት ስራዎቹን በጤናማ ሥነ-ልቦና እና በተረጋጋ መንፈስ ማከናወን ላይ ችግር የሚፈጥሩ እና ህይወቱን በእጅጉ የሚያመሰቃቅሉ ናቸው። ●የዕለት ተዕለት ተግባሮቻቸውን ለማከናወን ይሳናቸዋል።
●ሰዎችን በራሳቸውም ሆነ በሌሎች ሰዎች ላይ አሉታዊ የሆኑ ውጤቶችን እንዲያስከትሉ የሚያደርጉ ናቸዉ።

● በአጠቃላይ ችግሮች ያሉባቸው ሰዎች የሚኖራቸው የግል፣ የማህበራዊና የስራ ህይወት የተዛባ ይሆናል።

● ስለዚህ የህግ ታራሚዎች እና የቀጠሮ እስረኞች ለችግሩ ከመጋለጣቸው በፊት **የሥነ-ልቦናዊ ችግሮችን መንስኤ፣ መከላከያና መፍትሄ የሚሆኑትን ነጥቦች አስቀድሞ በመረዳት ራሳቸውን ከችግሩ ለመጠበቅ እንዲችሉ** በምክክር አገልግሎት ባለሙያዎች የቅድመ መከላከል የምክክር አገልግሎት ግንዛቤ ሊፈጠር ይገባል።

● **የቅድመ መከላከል የምክክር አገልግሎት** ታራሚዎች ለተለያዩ የሥነ-ልቦና ቀዉሶች ሊያጋልጡ የሚችሉ ጉዳዮችን **አስቀድሞ በማሳወቅና በማስገንዘብ ለችግሮቹ እንዳይጋለጡ ያደርጋቸዋል፣ ያረጋጋቸዋል።**

2.2 የግል (የተናጥል) የምክክር አገልግሎት

● የተናጥል የማረም ካውንስሊንግ አገልግሎት ከሌሎች ታራሚዎችና እስረኞች በተለየ መልኩ የስነ-ልቦና ቀውሶች ሲያጋጥም የሚደረግ የአገልግሎት ሂደት ነው።

● ሰዎች የተለያዩ እንደመሆናቸው መጠን ችግሮቹም የተለያዩ ይሆናሉ። ለምሳሌ ለመጥቀስ ያህል ከፍተኛና ከእውነታ ጋር ያልተገናኘ መጠነ ሰፊ የአእምሮ ቀውስና ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሱ የስብዕና ቀውሶች ያሉባቸው እስረኞችና ታራሚዎች በተናጥል የካውንስሊንግ አገልግሎት ቢረዱ የተሻለ ውጤት ይገኛል።

social worker indevisal service

1.preparing
2.Begning
3.Exploring
4.Assesing
5.Contracting
6.Working and evaluation
7.Ending if this not given solution refer system
(pleasure and pine calculation እያመመንም ቢሆን የምንሰማው)

Psychological spectrum disorder

1. Delustion (false believe not real one)

- ሌሎች ሰዎች እየተከታተሉኝ ነው ይላሉ እውነቱን ብታስረዶቸው አይሰሙም
- ሁሉን ነገር ማድረግ እንደሚችሉ ያስባሉ
- ውሎቸው እና አዳራቸው ከትልልቅ ሰዎች ጋር እንደሆነ ይናገራሉ
- ሰዎች ሁሉ ስለነሱ የሚያወሩ ይመስላቸዋል
- በጣም ተጠራጣሪዎች ናቸው
- ሁሉም ሰው እንደሚወዳቸው አብዝተው ይናገራሉ ።

Hallucination

- በትክክል ከምነቀው ውጭ መረጃ አላቸው
- የሌለ ነገር ያያሉ ይሰማሉ ለምሳሌ የሌለ ድምፅ መስማት መሳቅ መሬት መሬት ማየት ለምሳሌ ሰውነታችን ውስጥ እንሰሳ አለ ወዘተ
- dis organized thought In coherent speech

1. Negative symptom (የሚያስቅ የሚያሳዝን የሚያስፈራራ ነገር ሲያዩ ምንም ስሜት አይሰማቸውም ለምሳሌ ሰርግ ላይ ማልቀስ ፡ፍቅር ላይ ስሜት አልባ መሆን

Motor disturbance

- ለረጅም ጊዜ አንድ ቦታ መቆም (አለመንቀሳቀስ)
- እኔ ከዚህ በሃላ ማንንም አልጠቅምም ብሎ ማለት
- ከቤት መውጣት መጫወት አለመፈለግ ሶስት ሳምንት ከቆየ ምርመራ ያስፈልገዋል ።

❑ Anxiety disorder types 4.selective disorder
1.genral anxiety disorder 5.phobia
2.panic disorder (ቅፅፈታዊ ከ 4-6 ደቂቃ
3.separartion anxiety disorder
6.trauma related disorder የፃታ ጥቃት በመጥፎ የመኪና አደጋ ዘመድ ጉደኛ ሞት 7.somatic disorder ሰዎች ያለምንም ምክንያት ፓራላይዝድ መሆን ። (malangrine)

Steps of the correction counseling process

1.Establishing the relationships
2.Stracturing the counseling r/s
3.Psycological assessment(ስነ ልቦናዊ ግመታ)
4.Psycological diagnosis
5.Prognosis
6.Treatment a.cognative therapy(ግንዛቤ ማስጨበጫ)
b.behavioural therapy eg vandalizm
c. systematic systemization eg socialization
7.Follow up
8.Evaluation

- **በከፍተኛ የአዕምሮ ቀውስና ችግር** ውስጥ ላሉት ታራሚዎችና የቀጠሮ እስረኞች ከጋራ የካውንስሊንግ አገልግሎት ይልቅ የተናጥል ወይም የአንድ ለአንድ የካውንስሊንግ አገልግሎት የበለጠ ውጤታማ እንደሆነ ጥናቶች ይጠቁማሉ።
- የተናጥል የምክክር አገልግሎት ታራሚዎች ከባለሙያዎች በሚያገኙት የምክክር አገልግሎት ከገቡበት የሥነ-ልቦና ችግሮች **(ከጭንቀት፣ ከድብርት፣ ከንዴት፣ ከስጋት፣ ከዉጥረት፣ ከቁጡነት ስሜት፣ ከፍርሃት፣ ከድንጋጤ፣ ከብስጭት፣ ከስሜታዊነት፣ ከጨለምተኝነት፣ ወዘተ)** ተላቀው የተረጋጋና ሠላማዊ ህይወት መኖር እንዲችሉ ያደርጋቸዋል።
- ለመታረምና ለመታነፅ ዝግጁ ይሆናሉ፣ይነሳሳሉ።

2.3 የቡድን የምክክር አገልግሎት

የቡድን የማረም ካውንስሊንግ አገልግሎት፡-

● ተመሳሳይ የስነ ልቦና ችግር ያሉባቸው (ከጭንቀት፣ ከድብርት፣ ከንዴት፣ ከሰጋት፣ ከውጥረት፣ ከቁጡነት ስሜት፣ ከፍርሃት፣ ከድንጋጤ፣ ከብስጭት፣ ከስሜታዊነት፣ ከጨለምተኝነት፣ ወዘተ)

● የአደገኛ ዕፆችና መድሃኒቶች ሱሰኝነት ችግር፣

● ወሲባዊ ጥቃት የመፈጸም ስነ- ልቦናዊ ቀውሶች ያለባቸዉን ታራሚዎች ቡድን መስርተዉ በጋራ ችግሮቻቸዉ ላይ በጥልቀት በመወያየት በችግሮቹ ምክንያት ከሚያጋጥማቸዉ የተለያዩ ሥነ-ልቦናና ማህበራዊ ችግሮች ተላቀው የተረጋጋና ሠላማዊ ህይወት መኖር እንዲችሉ ያደርጋቸዋል።

● የሚሰጠውም በማረሚያ ቤቶች ውስጥ ሲሆን ዋና አላማው ተገልጋዮቹ ያሉባቸውን ችግሮች በማንሳት በካውንስለሩ ድጋፍና የእርስ በርስ ድጋፍ ለችግሮቻቸው መፍትሄ የሚፈለግበት ነው።

ይህን የካውንስሊንግ አገልግሎት ዓይነት በማረሚያ ቤቶች መጠቀም በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት።

●ታራሚዎችና እስረኞች እርስ በርስ ለመረዳዳት፣ ለመማማር፣ ማህበራዊ ክህሎቶችን ለማዳበርና ብቸኝነትን ለመከላከል ጥሩ አጋጣሚዎችን ይፈጥራል።

● አገልግሎቱን የሚሰጡ ባለሙያዎች የታራሚዎችን ደህንነት በማስጠበቅና የሚስጥር አጠባበቅ ሁኔታዎች ላይ ትኩረት ማድረግ ይኖርባቸዋል።

ለምሳሌ ሁሉም የቡድኑ አባላትና ባለሙያው **በካውንስሊንግ ሂደቱ ወቅት የተነሱ ነገሮችን በምስጢር መያዝ** ይኖርባቸዋል።

- **የተሳታፊዎች ፈቃደኝነትም** መኖር አለበት። ለዚህ ደግሞ የማነሳሳት ስራ መሰራት አለበት።
- የካውንስሊንግ አገልግሎት **ሂደቱን ተገቢ ደንቦችን በማውጣት ማስኬድ** ያስፈልጋል።
- የባለሙያው ሚና **በቡድን አባላቱ መካከል ጤናማና ተገቢ የሆነ ግንኙነት እንዲኖር ማድረግ** ነው።

2.4 የአቻ ለአቻ የምክክር አገልግሎት

- ማረሚያ/ማረፊያ ቤቶች የተለያዩ ሰዎች የሚቆዩበት እንደመሆኑ መጠን **የተማሩ፣ እውቀትና ክህሎት ያላቸውና በተለያዩ መስኮች ልምድ ያካበቱ** ታራሚዎችና የቀጠሮ እስረኞች ይገኛሉ።
- በመሆኑም እነዚህን ሰዎች የካውንስሊንግ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ እና **እውቀታቸውን፣ ክህሎታቸውንና ልምዳቸውን መጠቀም** አስፈላጊ ነው።
- ሰራውን እንዲያግዙ ማድረግ ያስፈልጋል።

- የአቻ ካውንስሊንግ አገልግሎት ሰጭዎችን ለመጠቀም **በአግባቡ መምረጥና ማሰልጠን** ያስፈልጋል።
- አገልግሎቱን ለመስጠት **ያላቸው ፍላጎት፣ እውቀትና ክህሎት መታየት** አለባቸው።
- የአቻ ለአቻ የምክክር አገልግሎት በሌሎች የካውንስሊንግ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ትኩረት መሰጠት ያሉባቸው ነገሮች በሙሉ ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው።
- የአቻ ለአቻ የምክክር አገልግሎት ታራሚዎች **ችግሮቻቸውን እርስ በርሳቸው በመወያየትና በመረዳዳት ችግሮችን በጋራ እራሳቸዉ የመፍታት ክህሎታቸዉ ጨምሮ የተረጋጋና ሰላማዊ የሆነ የእርምት ጊዜን ማሳለፍ እንዲችሉ** ያደርጋቸዋል።

ለህግ ታራሚዎችና እስረኞች የምክክር አገልግሎት መስጠት አስፈላጊነት

- በማረሚያ/ማረፊያ ቤቶች ውስጥ ያሉ **ስነ-ባህሪያዊና ማህበራዊ ችግሮች ያሉባቸው** የህግ ታራሚዎች መብዛትና የአገልግሎቱ ተፈላጊነት በተገልጋዮቹ ፍላጎት እየጨመረ የመምጣት ሁኔታ ይታያል።
- በመሆኑም በማረሚያ ቤቶች የምክክር አገልግሎትን ለህግ ታራሚዎችና ለቀጠሮ እስረኞች መስጠት ካስፈለጉበት ምክንያቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ እንደሚከተለው ቀርቧል፦

- በርካታ ቁጥር ያላቸው የህግ ታራሚዎች የስነ-ባህሪና ማህበራዊ ችግሮች ያሉባቸው በመሆኑ እነዚህ ታራሚዎች ከችግሮች እንዲወጡ፤
- የህግ ታራሚዎች ወደ ወንጀል እንዲገቡ የሚገፋፋቸው የራሳቸው የሆነ ያልተስተካከለ ስሜት፤ ስብዕና፤ አስተሳሰብ፤ የኑሮ ዘይቤ ወዘተ ሊሆን ስለሚችል ታራሚዎቹ ከእነዚህ ችግሮች እንዲላቀቁ፤
- የማረሚያ ቤት አከባቢያዊ ሁኔታና አኗኗር በራሱና ራሳቸውን በማረሚያ ቤት ውስጥ በማግኘታቸው ምክንያት ታራሚዎች ስነ-ባህሪያዊና ማህበራዊ ችግሮች ሊታዩባቸው ስለሚችል፤

● በሌላ በኩል ደግሞ የማረሚያ ቤቶች **አካባቢያዊ ሁኔታ፣ አያያዝና አስተዳደር** ከሌሎች ለምሳሌ **ከቤተሰብ፣ ከሥራ፣ ከትምህርት ቤት፣ ወዘተ አካባቢያዊ ሁኔታዎች ለየት ያሉ** በመሆናቸው ታራሚዎችና የቀጠሮ እስረኞች ራሳቸውን ከዚህ የማረሚያ ቤቶች የእኗኗር ዘይቤ ጋር ራሳቸውን ለማስማማት ሊቸገሩ ይችላሉ፣

በመሆኑም ለተለያዩ **ስነ-ባህሪያዊ ችግሮች** ይጋለጣሉ።

● ይህም ሁኔታ ለህግ ታራሚዎችና ለቀጠሮ እስረኞች የካውንስሊንግ አገልግሎት አስፈላጊ መሆኑን ያሳያል።

በአጠቃላይ በማረሚያ ቤቶች ውስጥ የካውንስሊንግ አገልግሎትን አስፈላጊነት የሚያሳዩ ምክንያቶች ብዙ ቢሆኑም በዋነኛነት ግን ሁለት ነገሮችን መሠረት ያደረገ ነው።

- የመጀመሪያው **የወንጀል ተጋላጭነትን በመቀነስ ወንጀልን ለመከላከል** ሲሆን
- ሁለተኛው ደግሞ በማረሚያ ቤት የሚገኙ የህግ ታራሚዎች **የስነ-ልቦና ድጋፍ** የሚያስፈልጋቸው በመሆኑ ነው።

ከአገልግሎቱ የሚጠበቅ ውጤት

- ካውንስሊንግ **ጤናማ የሆነ የስብዕና ዕድገት** (Personality Development) ማምጣት አንዱና ዋንኛ ግቡ ነው።
- በዚህ ዘርፍ በራስ መተማመንና የተሟላ የህይወት ስኬት ማስመዝገብ መቻል።
- ስሜታቸውን አውጥተው የማይናገሩ/ለሌሎች የማያካፍሉ ሰዎች በውስጣቸው አምቀው የያዙት ችግር ወይም የታፈነ ስሜት የከፋ ችግር ሳያመጣ በማውጣት መፍትሄ/ እፎይታ ማግኘት።

- ካውንስሊንግ **የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክም ጭምር** እንደሆነ ይገልጻሉ።
- በካውንስሊንግ ሂደት ተገልጋዮች (Clients) ስለራሳቸው **ጥንካሬና ድክመት ስለሉ ዕድሎችና ስጋቶች ግንዛቤ እንዲያገኙ** ያስችላቸዋል።
- አንዳንድ ሰዎች ህብረተሰቡንም ሆነ የራሳቸውን ህይወት አደጋ ላይ በሚጥሉ ተግባራት ይሰማራሉ። ለምሳሌ በሀሽሽ ንግድ እና በመሳሰሉት ይህ ዓይነቱ ሁኔታ የሚከሰተው ግለሰቦቹ ስለማህበራዊ ስርዓቱና ህግጋቱ በቂ ግንዛቤ ሳይኖራቸው ሲቀር ነው።
- በመሆኑም ካውንስሊንግ **የተስተካከለ አመለካከት እንዲፈጥሩ** ያግዛል።

በአጠቃላይ የህግ ታራሚዎችና የቀጠሮ እስረኞች ከተለያዩ የሥነ-ልቦና ችግሮች በመላቀቅ፡-

- **የባህሪ ለውጥ** ማምጣት፣
- **ባህሪን ማስተካከል** (ከአካባቢያዊ ሁኔታዎች ጋር ማጣጣም)፣
- **የተረጋጉና ሰላማዊ** ዜጋ መሆን፣
- **የስነ-ልቦና ጤንነት** እንዲኖር ማድረግ፣
- **የአስተሳሰብና የስነ-ምግባር ለውጥ** ማምጣት፣
- **ጤናማ የሆነ ህይወት** በማ/ቤት ውስጥ መኖር እንዲችሉ ማድረግ፣
- **ራስን መሆን** መቻል፣
- **ለችግር የማይዳርግና ተገቢ ውሳኔ መወሰን** መቻል፣

3. የንቃተ ሕግና ስነ - ምግባር ግንባታ ትምህርት

የንቃተ ህግ እና ስነ ምግባር ግንባታ ት/ት የህግ ታራሚዎችን እና የቀጠሮ እስረኞችን በህግ እና ስነ ምግባር ግንዛቤ እና በአደገኛ መድሃኒቶች እና እፆች አስከፊነት ዙሪያ ት/ት መስጠት እና አምራች እና ሕግ አክባሪ መሆን እንዲችሉ ለማድረግ የሚሰጥ አገልግሎት ነው።

3.1 የንቃተ ህግ እና ስነ - ምግባር ትምህርት

- ታራሚዎችና የቀጠሮ እስረኞች ከተጠያቂነት በጸዳ መልኩ ህጋዊነትን ተከትሎ መኖር እንዲችሉ፤
- የመልካም ስነ ምግባር ባለቤት በመሆን በልማት እና እድገት ውስጥ ተሳታፊ ብሎም ባለቤት እንዲሆኑ ለማስቻል የሚሰጥ አገልግሎት ነው።
- አገልግሎቱም በፍትሃብሔርም ሆነ በወንጀል ህግ
- ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት እስከ ተቋማት ደንብ እና መመሪያ፣ ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች አተገባበር ዙሪያ በዜጎች ላይ የግንዛቤ መፍጠር ስራ መስራት ነው።

የንቃተ ሕግና ሰነ ምግባር ት/ትን በማረሚያ ቤቶች ውስጥ ለሕግ ታራሚዎችና ለቀጠሮ እስረኞች በተጠናከረ መልኩ መስጠት የሚከተሉትን መሠረታዊ መርሆዎችና ጠቀሜታዎች ይኖሩታል።

1. **የሕግ ምንነት** (ሕግ- የሰዎችን የእርስ በርስ ግንኙነት ወይም ቡድናዊ ግንኙነት የሚቆጣጠር ደንብ መሆኑ)፣ **ሕገ መንግስታዊ ሕግ** (የሕጎች የበላይ ሕግ እና ከሌሎች ሕጎችም በላይ ለረዥም ጊዜ እንዲያገለግል ተብሎ የሚዘጋጅ መሆኑ)፣

የሰብዓዊ መብት ሕግ (የሰዉ ልጅ ሰዉ በመሆኑ ብቻ ሊያገኛቸዉ የሚገቡ መብቶች እና በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት ምዕራፍ ሶስት ማለትም ከአንቀጽ 14-28 ሙሉ በሙሉ ለሰብዓዊ መብቶች የተመደበ፣ የወንጀል ሕግና የታራሚዎች ሕጋዊ መብቶችና ግዴታዎቻቸውን አውቀው ለተግባራዊነቱ ድርሻቸውን እንዲወጡ፣ እና እኛም በኢፌዴሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 13 መሠረት በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የፌዴራል መንግስትና የክልል ሕግ አውጪ ሕግ አስፈፃሚና የዳኝነት አካሎች በህገመንግስቱ የተካተቱትን የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችና ድንጋጌዎች የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ ያለብን መሆኑ ተደንግጓል።

2.የቀጠሮ እስረኞችና የህግ ታራሚዎች መሠረታዊ የሆኑ የዲሞክራሲያዊ ስርዓት እሴቶችን አውቀውና ተግባራዊ የሚያደርጉ ብቁና ሀላፊነት የሚሰማቸው እንዲሆኑ ለማድረግ፣

3. ታራሚዎችና እስረኞች እንደ ዜጋ የአከባቢያቸውንና የሀገራቸውን ችግር ለመፍታት በፍቃደኝነትና በያገባኛል ስሜት ተሳትፎ እንዲያደርጉ የማብቃት ጠቀሜታ ይኖረዋል።

4. ለሀገራቸው **ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ተግባራዊነት ንቁ ተሳታፊ** የሚያደርጋቸው ግንዛቤ **አቅም** ይፈጥራሉ።

5. የማህበረሰቡን በጎ እሴቶችና ስነ ምግባር የመረዳት ባህላቸው ያድጋል።

የስነ ዜጋና ስነ ምግባር ት/ት እሴቶች የሚባሉትን ዲሞክራሲ፣ የህግ የበላይነት፣ እኩልነት ፍትሀዊነት፣ የሀላፊነት ስሜት የሀገር ፍቅር፣ ጠንካራ የስራ ባህል፣ ራስን መቻል፣ የቁጠባ ባህል፣ ንቁ ህዝባዊ ተሳትፎና እዉቀትን መሻት በመረዳት ግንዛቤ ያገኛሉ።

- በመሆኑም ውጤቶቹን ከእነዚህ ነጥቦች አንፃር መገምገም ይጠበቃል።
- መብታቸውን ለማስከበር ግዴታቸውን እየተወጡ ናቸው ወይ ብልን መፈተሽ አለብን።

3.2 በአደገኛ መድሃኒቶች እና እፆች አስከፊነት ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠት

● የአደንዛዥ እጽ ዝዉዉር በአለማችን ጎልተዉ ከሚታዩ ሀገ ወጥ ድርጊቶች አንዱ ነዉ። በርካቶችን ለወንጀል ከሚዳርጋቸዉ በተለያዩ ዕጾች የሱስ ተጠቂ መሆን ነዉ። የእጽ ተጠቃሚ መሆን የሰዎችን በአግባቡ የማሰብ ችሎታ በማዳከም የተዛባ ዉሳኔ እንዲወስኑ በማድረግ ወዳልተፈለገ ባህርይ እና ማንነት ይወስዳቸዋል። ለምሳሌ፡- ለኤች አይ ቪ ኤድስ፣ ለዘረፋ፣ ለቸልተኝነት፣ ቤተሰብን ማሸማቀቅና መበተን ፣ ለጤናና የአካል መቃወስ ፣ ለተስፋ መቁረጥና ራስን ማጥፋት ለመሳሰሉት ከሰዉነት ስብዕና እጅግ ለሚቃረኑና የሰዉ ልጅ ላልተፈጠረበት ርካሽ ስብዕናዎች በመዝፈቅ ሕይወትን የተመሳቀለ ያደርጋል።

● ባለሙያዎችም በተቻለ መጠን ከዚህ መፅዳት አለብን። ከዓለማችንን ያወጡናል።

● በተለይ ደግሞ በማረሚያ/ማረፊያ ቤት ካለዉ የታራሚ የተለያየ የባህሪ አይነት እና የግንዛቤ ደረጃ አንጻር ይህንን ትምህርት መስጠት የታራሚዎችን በማረሚያ/ማረፊያ ቤት ውስጥም ሆነ ከማረሚያ/ማረፊያ ቤት በኋላ በሚኖራቸው ጊዜ ከአደገኛ መድሃኒቶች ጋር በተያያዘ ጥንቃቄ የተሞላበት ተግባር እንዲያከናውኑ አቅም የመፍጠር ስራዎችን ለመስራት ታስቦ ነው።

ለህግ ታራሚዎች/ ቀጠሮ እስረኞች የአደገኛ መድሂኒቶችና እጾች አስከፊነት ማስተማር አስፈላጊነት

ስለ አደገኛ ዕፆችና መድሀኒቶች አስከፊነት ለቀጠሮ እስረኞችና የህግ ታራሚዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠት አስፈላጊ የሚያደርጉ በርከታ ምክንያቶች ቢኖሩም ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

- በማረሚያ ቤቶች ውስጥ ያሉ **ስነ-ባህሪያዊና ማህበራዊ ችግሮች ያሉባቸው የህግ ታራሚዎች መብዛት፣**
- **የእጾችና የአደገኛ መድሂኒቶች አስከፊነት እየጨመረ** መምጣት፣
- **በቀሪ ህይወታቸዉ ከዚህ ችግር እንዲላቀቁ፤** ወደ ሱሰኝነት ያልገቡት ከእነዚህ ጎጂ ድርጊቶች ራሳቸዉን እንዲቆጥቡ በማስገንዘብ ከኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ስነ - ልቦናዊ ቀዉሶች እንዲወጡ ያስችላቸዋል።
- ማረሚያ ቤት እያሉም የዕፆች ተጠቃሚዎችን በማጋለጥ **የተከለከሉ ነገሮች ወደ ማ/ቤት እንዳይገቡ ይከላከላሉ፤ ጥቆማ ይሰጣሉ።**
- የአገልግሎቱ ታራሚዎች በዚህ ምክንያት **ወንጀልን በድጋሚ እንዳይሰሩ በማድረግ ሊኖረው** የሚችለው ውጤቶች ናቸው።
- በአጠቃላይ ታራሚዎች ከሱስ ተጋላጭነት በመራቅ **ራሳቸዉን፣ ቤተሰባቸዉን፣ ማህበረሰቡን** እና ከፍ ሲልም **ሐገርን መጠበቅ** ይኖርባቸዋል።

4. በስፖርትና መዝናኛ አገልግሎት

● ስፖርትና መዝናኛ አገልግሎት በማረሚያ/ማረፊያ ቤት ውስጥ የሚሰጥበት አላማ አገልግሎቱን **በተደራጀ፣ ባልተቆራረጠና ቀጣይነት ባለው መልኩ በመስጠት** በታራሚዎች የሚፈጠሩትን **አካላዊ ፣ ስነ-ልቦናዊና ማህበራዊ ጫናዎች እንዲቃለልላቸዉ** ለማድረግ ነዉ።

● ስፖርትና መዝናኛ ከስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችና ጨዋታዎች በተጨማሪ የተለያዩ **ስነ-ጥበባዊ እንቅስቃሴዎችንም እንደ ሙዚቃ፣ ስነ-ፅሁፍ፣ ድራማና የመሳሰሉትንም** ያጠቃልላል።

● በስነ-ጥበባዊ አርት ተሰጥኦ ያላቸዉን ታራሚዎች **በማደራጀት ፈጠራቸዉን ጠብቀዉና አሻሽለዉ የእርምትና እስር ጊዜያቸዉን እስኪጨርሱ ድረስ ታራሚዎችን እንዲያዝናኑና ሙያቸዉን ጠብቀዉ እንዲፈቱ ሁኔታዎችን በማመቻቸት** ይከናወናል።

በኮሚሽኑ መቋቋሚያ አዋጅ 1174/2012 መሠረት
1/በማረሚያ ቤት ግቢ ውስጥ በግል ወይም በቡድን
እስረኛ ለጤንነቱ ተስማሚ የሆነ ስፖርታዊ
እንቅስቃሴዎችንየማድረግ መብት አለው።
2/ኮሚሽኑ በማረሚያ ቤት ግቢ ውስጥ አካላዊ እና ስፖርታዊ
እንቅስቃሴዎች የሚያደርጉበት በቂ የሆነ ክፍት ቦታ ያዘጋጃል።
3/ኮሚሽኑ ከውጭው ማህበረሰብ ጋር ግንኙነት በመፍጠር
በተቻለ መጠን ለእስረኞች የባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ስፖርታዊ እና
መሰል የመዝናኛ መሰናዶ
እንደሚያደርግ ያብራራል።"

4.2 በማረሚያ ቤት ዉስጥ የሚዘወተሩ የስፖርትና መዝናኛ እንቅስቃሴዎች

1.የኳስ ጨዋታዎች

- እግር ኳስ፣
- ቮሊቦል፣
- ቅርጫት ኳስ፣
- ጠረጴዛ ኳስ፣

2. የቤት ዉስጥ ጨዋታዎች

- ቼስ፣
- ዳማ፣
- ዶሚኖስ፣
- ገበጣ ወዘተ፣

3. የባህል ስፖርቶች

- ገመድ ጉተታ ውድድር፣
- የጆንያ ዉስጥ ሩጫ ዉድድር፣
- የእንቁላል በማንኪያ ዉድድር፣
- ገበጣ ዉድድርና ጨዋታ ወዘተ፣

4. የማስ-ስፖርት

5. ስፖርታዊ ያልሆኑ መዝናኛዎች

- ሙዚቃና ውዝዋዜ፣
- ስነ-ፅሁፍ / መነባንብ፣ ግጥም፣ ልብወለድ/፣
- ድራማ፣

6. የሚዲያ አገልግሎቶች

4.3 በማረሚያ ቤት ዉስጥ የስፖርትና መዝናኛ እንቅስቃሴ አለማዎች

- ታራሚዎችና የቀጠሮ እስረኞች በስፖርት እንቅስቃሴ ማህበራዊ ግንኙነታቸዉን እንዲያሻሽሉ፣
- ታራሚዎችና የቀጠሮ እስረኞች ከእንቅስቃሴ ጉድለት የሚመጡ በሽታዎችን እንደ አስም፣ ደም ግፊት፣ ጭንቀት፣ የደም ስብ መብዛት፣ ስኳር፣ ከፍተኛ ክብደት መጨመር፣ ከመጠን በላይ ዉፍረት ወዘተ መከላከል እንዲችሉ፣

● ስፖርተኛ ታራሚዎችና የቀጠሮ እስረኞች የእስር ጊዜያቸዉ እስኪያበቃ ብቃታቸዉ ተጠብቆ እንዲቆዩ ከማድረግ ባሻገር የስፖርት ውድድሮችን፣ ፌስቲቫሎችንና ጨዋታዎችን በተሻለ መልኩ በማንቀሳቀስ ጤናማ፣ ብቁና በእንቅስቃሴ ተሳታፊ ታራሚዎችንና የቀጠሮ እስረኞችን ማፍራት ነዉ።

● የተለያየ ችግር ያለባቸዉን ታራሚዎችና የቀጠሮ እስረኞች ለምሳሌ፡- ሱሰኞች፣ የብቸኝነት ባህሪ ወዘተ ተጠቂ የሆኑትን ወደ ምክክር፣ ትምህርትና ስልጠና፣ በልማት ስራና ማቋቋም በማደራጀት ቅድመ ሁኔታን በስፖርት እንቅስቃሴ ማመቻቸት እንዲቻል ለማድረግ፣

● ስፖርታዊ ባልሆኑ መዝናኛዎች/ በስነ-ፅሁፍ፣ በድራማና በሙዚቃ / ታራሚዎችና የቀጠሮ እስረኞች እንዲዝናኑና ክህሎታቸውን እንዲያዳብሩ ወዘተ ለማድረግ ነዉ።

● አዲስ ገቢ ታራሚዎች ራሳቸዉን መግለፅ እንዲችሉና ነፃነት እንዲሰማቸዉ፣ ዉጥረት እንዲቀንስላቸዉ፣ ከሌሎች ታራሚዎችና ከማረሚያ ቤት ህይወት ጋር እንዲዋሃዱና እንዲተዋወቁ ያደርጋል (as an adjustment tool)

● ታራሚዎች ለማረሚያ ቤት የሚኖራቸዉን ጥሩ እይታ ይጨምራል ፡- የማረምና ማነፅ አገልግሎትን የተሳለጠና ምቹ የታራሚዎችን ስነ-ምግባር ለማግኘት እንደማበረታቻ ያገለግላል።

- ታራሚዎች በማረሚያ ቤት ዉስጥ **የሚሰጣቸዉን ስራ ሁሉ እንደቅጣት እንዳይቆጥሩት** ያደርጋል። ማረሚያ ቤትን በመጥፎ እንዲያዩት አያደርግም።
- ተቋሙ **ለመደኃኒት የሚያወጣዉን ወጭ** ይቀንሳል።
- ታራሚዎች በእንቅስቃሴ ጉድለት ለሚከሰቱ በሽታዎች ስለማይጋለጡ በጭንቀት፣ በድብርት፣ በከፍተኛ ውፍረት ወዘተ ለሚከሰቱ በሽታዎች ህክምና የሚወጣውን የመድሃኒት ወጭ ይቀንሳል።

የስፖርት ፕሮግራሞች ሲታቀዱ ታራሚዎችን ወደ አገልግሎት ከማስገባታችን በፊት የሚከተሉትን ሂደት ማለፍ ተገቢ ነው።

- የታራሚዎችን **የጤና ሁኔታ መጠየቅና ማጣራት፣**
- የታራሚዎችን **የስፖርት የኃላ ታሪክ በማጣራት ያላቸውን ልምድ ማወቅ፣**
- የታራሚዎችን የግል ፍላጎት መሰረት በማድረግ ቀስ በቀስ ወደ **እንቅስቃሴና ተሳትፎ ማሳሳትና ወደ አገልግሎቱ እንዲገቡ ማድረግ** ናቸዉ።

5. አገልግሎቶችን በትክክል ማቀድና መተግበር

በተቋም ደረጃ፦

- የአምስት አመት ስትራቴጅክ ዕቅድ አለን።
- ከዚህ በመነሳት **የአመት፣ የስድስት ወራት፣ የሶስት ወራት፣ የወር እና ሳምንታዊ የዉጤት ተኮር እቅዶች** ይዘጋጃሉ።
- እቅዶቹ በሚዘጋጁበት ጊዜ **የተቋሙን ራዕይ፣ ተልዕኮና ዓለማ ለማሳካት በሚያስችል መልኩ** ይታቀዳሉ።
- በዕቅዶቹ መሠረት **አገልግሎትን መስጠት** ይጠበቃል።
- ለአገልግሎቶቹ **የተዘጋጁ ማኑዋሎችን፣ ስታንዳርዶችን፣ መመሪያዎችን፣ አዋጆችን፣ ደንቦችን፣ ፖሊሲዎችን ህጎችን** መሰረት ማድረግ አለብን።

6. አገልግሎቱ ያመጡትን ውጤቶች (ለውጦች) ለማወቅ/ለመመዝገብ የሚደረግ ክትትልና ግምገማ (Follow up & Evaluation)

6.1 ክትትል ማድረግ (Follow up)

- የማረምና ማነፅ አገልግሎቶች (የማህበራዊ፣ የምክክር፣ የንቃተ ህግና ሰነ ምግባር ትምህርት እና የስፖርትና መዝናኛ አገልግሎት) **ከተሰጠ በኋላ ሂደቱ ያመጣውን ውጤት (የባህሪ ለውጥ፣ የግንዛቤ ደረጃ ወዘተ) መገምገም** ያስፈልጋል። አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ሙያዊ ግዴታም ነዉ።
- ውጤቱን ለማየት ደግሞ አገልግሎት ሰጪዎች የክትትል ተግባር ማከናወንን ይጠይቃል። ክትትሉም በሁለት መንገድ ሊካሄድ ይችላል።

- አንደኛው **አገልግሎቱ በመሰጠት ላይ እያለ** ወይም አገልግሎቱ ሙሉ በሙሉ ከመጠናቀቁ በፊት የሚደረግ ክትትል(**የእለት ተዕለት**) ሲሆን
- ሁለተኛው ደግሞ **የአገልግሎት ሂደቱ ሙሉ በሙሉ ከተጠናቀቀ በኋላ** የሚከናወን የክትትል ዓይነት ነው።

በአጠቃላይ ባለሙያዎች በክትትል ወቅት አገልግሎቱ ያመጣውን ውጤት ወይም ለውጥ ለማወቅ ከተለያዩ አካላት አገልግሎት ተቀባዩን (ታራሚዎችና የቀጠሮ እስረኞች) ጨምሮ መረጃዎችን ማሰባሰብ ያስፈልጋል።

- መረጃውን ደግሞ በተለያዩ መንገዶች ማግኘት ይቻላል።
- **የባለሙያው የራሱ ምልከታ** (የሰጠዉን አገልግሎት ከተቀመጠለት ዉጤት ጋር ታራሚዉ/እስረኛው ላይ የሚታየዉን ለዉጥ በማነፃፀር)፣
- **በተገልጋዩ ዕይታ** (ታራሚዉ በራሱ ላይ ያየዉን ለዉጥ ተከታትሎ በመጠየቅ)፣
- ሌሎች የቅርብ አካላትን ለምሳሌ፦
- ከዞን ኃላፊዎች፣ ከቤት ተከታታይ ኦፊሰር
- ከጓደኞች፣
- ከቤት አስተዳደሮች፣
- ከ1 ለ 10 መሪዎች፣
- ከታራሚዎች አደረጃጀት፣ ወዘተ በመጠየቅ ስለ ለውጡ በቂ መረጃዎችን ማግኘት ይቻላል።

በዚህ መልኩ መስራትም ይጠበቃል።

6.2 ግምገማ ማድረግ (Evaluation)

● የአገልግሎቶቹ ውጤታማነት የሚታወቀውና የሚረጋገጠዉ ተገቢ የሆነ ግምገማ ሲካሄድ ነው። በግምገማ ጊዜ ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ ነጥቦች፡-

● የአገልግሎቶቹ **የግንኙነት ሂደቱን**፣ (ጥሩ ግንኙነት መመስረቱን ለምሳሌ ስለአገልግሎቱና ከአገልግሎቱ የሚጠበቀዉ ውጤት ዙሪያ በትክክል መግባባት ላይ መደረሱና ለዉጤቱ መምጣት በጋራ መንቀሳቀሱ)፣

● ለአገልግሎቶቹ **ተገቢዉ ዓለማ፣ ግቦችና የሚጠበቁ ዉጤቶች** ስለመለየታቸው፣

● **በቂ መረጃ መሰብሰቡን** (የወንጀል አይነት፣ የፍርድ ልክ፣ ዕድሜ፣ የት/ት ደረጃ፣ የጤና ሁኔታ፣ ፍላጎት ወዘተ በትክክል መሰብሰብና መደራጀት አለበት)፣

- የችግሩ ሁኔታ ከተሰበሰበው **መረጃ በትክክልና በአግባቡ መጨመቁን፤**
- ትክክለኛ **የችግሩ ምንነትና መንስኤዎች** ላይ መደረሱን ማረጋገጥ፣
- ለመፍትሔው አስፈላጊና ተገቢ ንድፈ-ሀሳቦችና ስልቶች መመረጣቸውንና መተግበራቸውን፣
- ከተተገበሩ በኋላ ዉጤቱን ለመገምገም ክትትል በበቂ ሁኔታ መካሄዱን በተመለከተ **ግምገማ ማካሄድ** ያስፈልጋል።

በአጠቃላይ ግምግማው አገልግሎት የተሰጣቸውን ተገልጋዮች ከአገልግሎቱ በ□ላ ማምጣት የሚጠበቅባቸዉን ለዉጦች (ዉጤት) ለምሳሌ ባህሪያቸው፣ ስሜታቸው፣ አመለካከታቸዉ፣ አስተሳሳባቸው፣ ስብዕናቸው፣ ስለ ሰላማዊ ግንኙነታቸዉ፣ የአካልና የጤና ሁኔታቸዉ፣ ስለፈፀሙት ወንጀል መፀፀታቸዉ ወዘተ የተለያዩ የማህበራዊ፣ የስነ-ልቦና፣ የህግ እና የስፖርትና መዝናኛ አገልግሎት የባህሪ ለውጥ መለኪያዎችን በመጠቀም መለካትና እነዚህ የማረምና ማነፅ አገልግሎቶች ከመሰጠቱ በፊት ከነበረባቸው የችግር፣ ሁኔታና ደረጃ ጋር በማወዳደር ይካሄዳል። ለዚህ ሁሉ መረጃን በአግባቡ መያዝና ማደራጀት ያስፈልጋል።

7. ስለመረጃ አመዘጋገብና አያያዝ (Documentation and Record Keeping)

7.1 መረጃን መዝግቦ የመያዝ ጥቅም ፡-

- በመጀመሪያ ደረጃ መረጃን መዝግቦ መያዝ **ጥቅሙ ለአገልግሎት ሰጭውና ለአገልግሎት ተቀባዩ** ሲሆን ይህም፡-
- ስለሚሰጠው አገልግሎት **ዕቅድ ለማዘጋጀት መሠረት** ይሆናል፣
- **ትክክለኛውን አገልግሎት ለመስጠት** ያስችላል፣
- ባለሙያው **የሚሰራውን ሥራ ለመቆጣጠር** ያስችላል፣
- የተገልጋዮችንን **ለውጥ ለመከታተል** ያስችላል፣
- መረጃን መዝግቦ መያዝ **ለሦስተኛ ወገንም ስለአገልግሎቱ በቂ የሆነ ግንዛቤ** ይሰጣቸዋል።

በአጠቃላይ አስፈላጊውን መረጃ መዝግቦ፣ አደራጅቶና ፋይል አድርጎ የመያዝ አስፈላጊነቱ ለሦስት ዋና ዋና ምክንያቶች ነው። እነሱም፡-

1. አገልግሎቱ ቀጣይነት እንዲኖረው (Continuity of services)፡-

- ትክክለኛ (Accurate) እና ወቅታዊ (up-to-date) የሆነ መረጃን አደራጅቶ መያዝ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። ይህም፡-
- የተገልጋዮቻችንን **ጉዳይ ወይም ታሪክ ሰፋ ያለ ግፅታ** እናገኛለን፣
- የሚሰጠውን አገልግሎት **ለመከታተል ወይም ተገልጋዮቻችንን በተለያየ መንገድ ለመርዳት** ያግዘናል፣

● ሌላው መረጃ ለአስቸኳይ ጉዳይ በሚፈለግበት ጊዜና ባለሙያው በተለያዩ ምክንያቶች (ለምሳሌ፡- በህመም፣ በእረፍት፣ ሥራን በመልቀቅ) በማይገኝበት ጊዜ ተደራጅቶ ከተቀመጠው መረጃዎች በመነሳት አገልግሎቱን ማስቀጠል ይቻላል።

● በጥሩ ሁኔታ የተመዘገበና የተያዘ መረጃ በአገልግሎት ሰጭውና አገልግሎት ተቀባዩ መካከል ታአማንነትና ጥሩ መግባባት እንዲኖር በማድረግ በአገልግሎቱ ዙሪያ መልካም የሆነ ትስስርን ይፈጥራል።

2. አገልግሎትን ለማሻሻል (Service improvement)

● በጥሩ ሁኔታ ተመዝግቦ የተያዙ መረጃዎች ካሉ ባለሙያው በተደራጀ ሀሳብና መረጃ ለተገልጋዩ የሚሰጠዉን አገልግሎት ለማሻሻል ይረዳል።

● የተደራጀ የተገልጋዮቻችን መረጃ ካለ **የአገልግሎቱን ዕቅድ ለማዘጋጀት** (ዓላማ፣ ግብና ዉጤትን በትክክል በማስቀመጥ)፣ ●**የአገልግሎቱን ደረጃ ለማሳደግ እና አገልግሎቱን ለመገምገም** (በትክክል ከተቀመጠዉ ዓላማ፣ ግብና ዉጤት አንፃር) ይረዳል።

● በተጨማሪም የተሟላ መረጃ ካለ መረጃን **መሠረት ያደረገ የአገልግሎት አሰጣጥ ጥናት ለማካሄድና በዉጤቱ መሠረት አገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል** እንደ መጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምንጭ ያገለግላል።

3. ተጠያቂነት እንዲኖረው ለማድረግ (Accountability)፡-

- ተጠያቂነት አስፈላጊነቱ አገልግሎት ሰጪው አካል የተገልጋዮችን ጠቃሚ መረጃ በማንኛውም ጊዜ እንዲያሳይ በሚጠየቅበት ማሳየት የሚችልና ተቋሙ ለተገልጋዮቹ የሚፈልጉትን አገልግሎት እንዴት ማቅረብ እንዳለበት የሚያሳይ ሲሆን፡-
- መረጃው የሚያካትተው እንደ አስፈላጊነቱ የባለድርሻ አካላትን እገዛ ለምሳሌ የታራሚዎችን ቤተሰቦች፣ የበጎ አድራጊ ድርጅቶችን፣ የፍርድ ቤት ውሳኔ ወዘተ ያካትታል።
- አንዱ በጣም አስፈላጊው የመረጃ ምንጭ የታራሚዎች ሪከርድ/ማህደር/ ነው።
- በተጨማሪም በተቋሙ ውስጥ የሚሰሩ ሙያተኞች ከታራሚው ጋር በሚያደርጉት ግንኙነትና አገልግሎት አሰጣጥ ወቅት መረጃ ማግኘት ይቻላል።
- የተገኙ መረጃዎችና ችግሮች በተቋሙ አሰራር መሰረት **መፈታትና እልባት መሰጠት** አለባቸው።

7.2 ፋይል የሚደረጉ ነገሮች ምንድን ናቸው?

የተገልጋዮች መረጃ በሚያዝበት ወቅት ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ ዋና ዋና ነጥቦች፡-

- የተገልጋዮች የተፈጥሮ ልዩነት መጠን፣
- የተገልጋዮቻችን ፍላጎቶች ውስብስብነት፣
- ተገልጋዮች ከአገልግሎቱ የሚጠብቁት ውጤት

እና የመሳሰሉት መረጃዎች ፋይል ተደርጎ ይያዛሉ።

በአጠቃላይ ፋይል መደረግ ያለባቸው ነገሮች፡-

- የተገልጋይ **ታሪክና ፍላጎቶች** (History and needs of client)፣
- ለአገልግሎቱ **የሚያስፈልጉ ነገሮች** (Services rendered)፣
- **የአገልግሎቱ መረጃ** (Programme information)
- **በተገልጋዩ የመጣው ለውጥ** (Client outcomes)፣

7.3 መረጃን ለመያዝ የሚረዱ መልካም ተሞክሮዎች (Best Practices for Documentation)

መረጃዎችን በምንይዝበት ጊዜ መረጃዎቹ ቀጣይነት እንዲኖራቸው የሚከተሉት ነጥቦች ላይ ትኩረት ሊንሰጥባቸው ይገባል።

እነዚህም፦

- መረጃው ቀጥተኛ መሆኑን ማረጋገጥ (Concise)፦ ይህም የተገልጋዮቻችን መረጃ ቀጥተኛና ዝርዝር መረጃ መሆን አለበት። ይህ መረጃም ከምንጠብቀው የተገልጋያችን የአገልግሎት ውጤት (ለውጥ) ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ብቻ መሆን አለበት።
- መረጃው ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥ (Accurate)፣
- መረጃው ወቅታዊ መሆኑን ማረጋገጥ (Up-to-date)፣
- መረጃው ትርጉም ያለው መሆኑን ማረጋገጥ (Meaningful)፣
- የተሟላ መረጃ መያዙን (Internally Consistent)፣

በአጠቃላይ ተሟላ መረጃ አደራጅቶ በመያዝና መረጃን መሠረት ያደረገ አገልግሎት መስጠት ይጠበቅብናል።

8. የሪፖርት አቀራረብ

- በሳምንት፣ በወር፣ በየሩብ ዓመት፣ በስድስት ወራት፣ በዘጠኝ ወራት እና በዓመት ሪፖርት **ይዘጋጃል፤ በመገምገም ለቅርብ ሀላፊ በወቅቱ ይለካል።**
- ሪፖርት ሲላክ **ወቅታዊ መሆን** አለበት።
- የሚላኩ ሪፖርቶች **ጥራት ሊኖራቸዉ** ይገባል።
- ከዕቅድ ጋር **በትክክል ተነፃፅሮ መላክ** አለባቸዉ።
- ሪፖርቱ **የተሰራውን ሥራ በግልጽ የሚያሳይ መሆን** አለበት።
- አገልግሎቱ **ያመጣውን የባህሪ፣ የአመለካከት፣ የአስተሳሰብ፣ የስብዕና ወዘተ ለውጥ በተጨባጭ የሚገልጽ መሆን** አለበት።
- ለውጡቹ **መገምገም መቻል** አለበት።

9. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች፡-

I● **የሀብት እጥረት** ለምሳሌ፡- የአገልግሎት መስጫ (የስልጠና መስጫና የቢሮ)፣ የቢሮ ወንበሮች፣ ጠረጴዛ፣ ሼልፍ፣ ኮምፒዩተር ወረቀት፣ የሚኒሚዲያ ቁሳቁሶች፣ የስፖርትና መዝናኛ ቁሳቁሶች ወዘተ

II● **የታራሚዎች ባህሪና አመለካከት ችግሮች፡-**

ከተቀጠርንበት ዓላማ ውጪ በገንዘብ፣ በእውቀት፣ በልምድ፣ ወዘተ ሊያታልሉን የሚፈልጉ ይኖራሉ። (በህግ፣ በአሠራርና ለሙያ ስነ ምግባር በመገዛት ማለፍ)

እኛንና ሌሎች ታራሚዎችን ለማስፈራራት፣ ለማጭበርበር፣ ለማበሳጨት፣ ለማናደድ፣ ተስፋ ለማስቆረጥ፣ የሚሳደቡ፣ ስራን ለማወክ የሚሞክሩ፣ ስልጠና ቦታ ዘግይቶ የሚደርሱ፣ ቶሎ ለመውታት የሚጥሩ ወዘተ ይኖራሉ።

(በህግና በአሠራር ተጠያቂ ማድረግ፣ ባህሪያቸውንና አላማቸውን መረዳት፣ ለአገልግሎቱ በቂ ዝግጅት ማድረግ)

III● **ከነባር ባለሙያዎችና የፖሊስ አባላት፡-** የቅንጅትና መናበብ ችግሮች ሊያጋጥም ይችላል፣ ተስፋ ማስቆረጥ፣ እንቅፋት መሆን ወዘተ፣ የአመለካከት ችግሮች ለምሳሌ ለምሳሌ ምን ለውጥ ለማምጣት ነው? እኔ የተማርኩ፣ እኔ ደግሞ የተቋሙ ባለቤት ወዘተ **ሽኩቻዎችና መገፋፋቶች፣**

IV● ከአዳዲስ ባለሙያዎች የሚያጋጥሙ ችግሮች፡- ውጣ ውረዶችን ተጋፍጦ ከማለፍ ይልቅ በትናንሽ ችግሮች ተስፋ መቁረጥ፣ የተስፋ አስቆራጮችን ተልዕኮ ተሸካሚ መሆን፣ ትዕግስት ማጣት፣ ችግሮች አግዝፎ ማየት፣ የባለቤትነት ስሜት ማጣት፣ (መፍትሔው ከተቀጠርኩ ጀምሮ መ/ቤቱ የኔ ነው ማለት መቻል፣ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ለውጥን ማምጣት ይቻለልን መከተል)

V● የአካባቢው ማህበረሰብና የታራሚዎች ቤተሰብ

እይታ፡- በተቋሙ የነበሩ ችግሮችን መነሻ የተቋሙን ሠራተኛ ጨካኝ አድርጎ ማየት፣ የእኛን ስራ ዝቅ አድርጎ ማየት፣ መናቅ፣ የተከለከሉ ነገሮችን እንዲናስገባና እንዲናወጣላቸው መፈለግ ለምሳሌ ሞባይል፣ ሱስ አስያዥ እፆችንና መዲሐኒቶችን እንዲሁም ግብዓቶቻቸው፣ አፍራሽ ተልዕኮ ያላቸውን ፅሑፎች፣ መፅሐፍት ወዘተ፣ ተላላኪ ማድረግ ለአፍራሽ ተልዕኮ፣ የተቋም ሚስጥር እንዲናወጣ፣ ገንዘቦችን እንዲናስገባ ወዘተ

10. የተገለፀዉን ውጤት ለማምጣት ከሌሎች ዘርፎችና የስራ ክፍሎች ጋር መኖር ያለበት ቅንጅታዊ ስራዎች

ሀ. እንደ ማረም ማነፅና ተሃድሶ ልማት ስራ ዘርፍ

1 ከትምህርት እና ስልጠና ዳይሬክቶሬት ጋር ያለው ትስስር

- ታራሚዉ በአመለካከት፣ በባህሪ፣ በአስተሳሰብ ወዘተ ተቀርፆ ለትምህርትና ለስልጠና ዝግጁ እንዲሆን ማድረግ ይቻላል።
- በትምህርትና በስልጠና ሂደት የአመለካከት፣ የባህሪ፣ የአስተሳሰብ ወዘተ ችግር ያለባቸዉን ታራሚዎች ለመምከርና ለማረም ወደ ማረምና ማነፅ ባለሙያዎች መለክና መረጃ መቀባበል ይገባል።

● ታራሚው ለትምህርት እና ስልጠና ሲወጣ ለማምለጥ እና ለንብረት ብክነት የሚዳርጉ ተግባራትን እንዳይፈፅሙ፣ ፈፅሞ ከተገኙ በህግ ተጠያቂ እንደሚያደርጋቸዉ በጋራ ማስገንዘብ ይቻላል።

● ትምህርታቸዉን፣ ስራዎቻቸዉን፣ ንብረቶቻቸዉን፣ ጊዜያቸዉን በአግባቡ እንዲጠቀሙ የሚያስችል ስራን በጋራ መስራት ይጠበቃል።

● የመንግስትን የት/ት እና ስልጠና ፖሊሲን እና ስትራቴጂ ስለሚማር በትምህርት እና ስልጠና ላይ ተግባራዊ ሊያደርግ የሚችልበትን የአመለካከት አቅም መፍጠር ይቻላል።

● በዚህ ውስጥ ያለፉ እና ለመማር እና ለመሰልጠን ዝግጁ የሆኑትን ታራሚዎች መረጃ በመለዋወጥ የማስተማር እና የማሰልጠን ስራን መስራት ይቻላል።

● ህግን በማወቅ እና ከሀገር ፖሊሲ እና ስትራቴጂ ጋር መተሳሰርን ልማታዊ እና አምራች ዜጋ የሚሆንበትን የመማርና **የመሰልጠንን ጠቀሜታ ስለሚረዳ አምኖበት የመማር እና መሰልጠን ባህል** ይኖረዋል።

2. ከልማት እና ማቋቋም ዳይሬክቶሬት ጋር ያለው ትስስር

- ታራሚው ስለ መንግስት የልማት እና የእድገት ፖሊሲ በአግባቡ ስለሚረዳ ባገኘው ስልጠና መሰረት ተደራጅቶ ስለመስራት፣ ስለመቆጠብ እና ስራን በአግባቡ በመስራት ድህነት መቅረፊያ መሳሪያ ስለመሆኑ የግንዛቤ አቅም ይፈጥርለታል።
- በአጠቃላይ ስለ ስራ ክቡርነት እና መልካም ስነ ምግባር ስለሚማር ስራን ሰርቶ መኖር መልካም ስነ ምግባር መገለጫ በመሆኑ ሰርቶ መለወጥን እንጂ በህገ ወጥነት መክበርን ስለማይመርጥ የልማቱ ተሳታፊ መሆንን በስራ እና በልማቱ ተግባር በመሳተፍ ተጠቃሚነቱን በማረጋገጥ ማሳየት እንደ ህግ ታራሚነቱ ያስችለዋል።
- በዚህ ውስጥ ያለፉ እና ለመስራት እና ለመደራጀት ዝግጁ የሆኑትን ታራሚዎች መረጃ በመለዋወጥ የማደራጀት እና ስራ የማሰራትን ተግባር ማከናወን ይጠበቃል።

ለ. ከጥበቃ፣ ደህንነትና አስተዳደር ዘርፍ

● ከታራሚዎች ፍትህ አስተዳደር እና ጥበቃ ደህንነት ዳይሬክቶሬቶች፣ ዘርፍ ማስተባበሪያዎች፣ ቡድኖችና የማረሚያ ፖሊሶች ታራሚዎችና የቀጠሮ እስረኞች ለአገልግሎት (ለልዩ ልዩ ማህበራዊ ስልጠናዎች፣ ለምክክር፣ ለስፖርትና መዝናኛ) ሲፈለጉ **ጠንካራና ተከታታይነት ያለዉ የመረጃ ቅብብሎሽ** (ለምሳሌ የአዲስ ገቢዎች፣ የደጋጋሚዎች፣ አካል ጉዳተኞች፣ የእእምሮ ህሙማን ወዘተ ያለፈዉ የህይወት ታሪክ በወንጀል ዓይነት፣ በፍርድ ልክ፣ በቀሪ የእርምት ጊዜ፣ በት/ት ደረጃ፣ በቤተሰብ ሁኔታ፣ ወዘተ) እና **ቀልጣፋ የእጅባ ስራ** ይፈለጋል።

- በተሰጡት የማረምና ማነፅ አገልግሎቶች **ለጥበቃ ስራ የፈጠሩት ምቹ ወይም ምቹ ያልሆኑ ሁኔታዎች በትክክል በመከታተል** (ለምሳሌ የተረጋጋ የጥበቃ እና ደህንነት አገልግሎት እንዲኖር የሚያግዝ ታራሚን መፍጠር ስለመቻሉ)፣ **ስለመጡ የባህሪ፣ የአመለካከት፣ የአስተሳሰብ፣ የስብዕና ወዘተ ለዉጥ ዙሪያ** በቅርበት ተከታትሎና መረጃ በትክክል በመያዝ ለባለሙያዎች ማቀበልና የባለሙያዎችንም እንደግብዓት በመዉሰድ መከታተል፣
- የታረሙና የታነፁ ታራሚዎችን **በአመክሮ እና በይቅርታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ** መረጃ ላይ የተመሠረተ **የባህሪ ማምጣና ሙያዊ አስተያየትን በመቀባበል** ወዘተ አብሮ መስራት ይጠበቃል።

ሐ. ከመሠረታዊ ፍላጎት ዘርፍ

- መብታቸዉና ግዴታቸው ከማረጋጋት ጀምሮ ስለሚሰጣቸዉ መሠረታዊ ቁሳቁሶች ለምሳሌ እንደ አልጋ፣ ፍራሽ፣ ብርድልብስ ወዘተ፣ ህክምና መሳሪያዎች እና አገልግሎትን፣ የንጽህና አጠባበቅ ስርአቶችን እና የመጸዳጃ እና መመገቢያ ግልጋሎትን በሚያውክ መልኩ በማረሚ ቤት ውስጥ እንዳይንቀሳቀሱ፣ ንብረትን እንዳያባክኑ በጋራ ግንዛቤ መፍጠር ይጠበቃል።
- በህብረት ሱቅና መዝናኛ ክበባት እና የጋራ መገልገያ ቦታዎች አጠቃቀም ከኪራይ ሰብሳቢነት፣ ከፀብና ብጥብጥ የፀዳ እንዲሆን፣ ገቢዉንም ለመዝናኛ ቁሳቁሶች እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ወዘተ በጋራ መስራት ይቻላል።

- የአእምሮ ጤና ችግር ያለባቸዉ፣ ኤች አይ ቪ ኤዲስ ቫይረስ በደማቸዉ ዉስጥ የሚገኙ፣ በሳይካትሪስቶች የሚታዩ የስነ ልቦና ችግሮች፣ ዖታዊ ጥቃት የተፈፀመባቸዉ ታራሚዎች ወዘተ ዙሪያ አብሮ መስራት ይቻላል።
- ከእንቅስቃሴ ጉድለት የሚመጡ በሽታዎችን እንደ አስም፣ ደም ግፊት፣ ኩላሊት፣ ከልክ በላይ ዉፍረት፣ የጡንቻ መሟሸሽ ፣ ራስ-ምታት ወዘተ መከላከል ዙሪያ በጋራ መስራት ይጠበቃል።
- የማረምና ማነፅ አገልግሎቶችን በአግባቡ ለመስጠት መሠረተ ልማትና ቁሳቁስ የማሟላት ስራ (የቢሮ ግንባታ፣ ጥገና፣ የስፖርትና መዝናኛ አገልግሎት መስጫ ቦታዎች ማልማት ወዘተ) አብሮ መስራት ይጠበቃል።

መ. ከፋይናንስ ሰዉ ሀብት ዘርፍ

ከፋይናንስ ሰዉ ሀብት ከዳይሬክቶሬት እስከ ፈፃሚ ሠራተኞች ድረስ ያሉ አካላት

- ከእቅድ አስተቃቀድ እስከ አፈፃፀም ክትትል፣
- ለሚያስፈልጉ ግብዓቶች ፋይናንስ መመደብና ግዥዎችን በወቅቱ ማከናወን፣
- ለአገልግሎቱ በቂ የሰዉ ሀይል መመደብ፣ መቅጠር፣ ማሰልጠን ወዘተ ስራዎችን በትስስር መስራት ይጠበቃል።

